□□□□□□□ □□□□□ □□□□□□□□ □□□□□
□□□□□ □□□□ □□□ □□

የሰበር መ/ቁ 222991

ጥቅምት 2 ቀን 2015ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች፡- 1ኛ/ አቶ ለገሰ አብዲ ወ/አረጋይ
2ኛ/ ወ/ሮ ሙሉ አያኖ ያዬቻ } አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ኤፍሬም ወዳጅ ገብሩ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

መዝገቡ ለሰበር ችሎት የቀረበዉ የአዲስ አበባ የንግድ ም/ቤት የመደበዉ የግልግል ጉባኤ የሰጠዉን ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል በሰበር ችሎቱ እንዲታረም የአመልካቾች ጠበቃ በቀን 07/07/2014ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነዉ፡፡

ጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ ክርክሩ የተመጀመረዉ በግልግል ጉባኤ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ፤የአሁን አመልካቾች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡የክሱ ይዘት ባጭሩ አመልካቾች በአ/አ ከተማ ን/ስ/ላፍቶ ክ/ከተማ በወረዳ 11ክልል ዉስጥ ካላቸዉ ይዞታ በግምት 6,000ካ.ሜ አዋሳኙ የተገለጸዉን ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት ከባለሀብት ጋር በጋራ ለማልማት ከተጠሪ ጋር በቀን 01/05/2010ዓ.ም ዉል አድርገዋል፤ተጠሪም ቦታዉን ለማልማት ልዩ ልዩ ወጭ አዉጥቷል፤ አመልካቾች ይዞታዉን ለማስረከብ እና ሙሉ ዉክልና ለመስጠት የገቡትን ግዴታ ለመወጣት ፈቃደኛ ባለመሆናቸዉ እንደዉሉ እንዲፈጽሙ

እና ሁከት እንዲያቆሙ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን አመልካቾች በበኩላቸዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ እና በፍሬ ነገር ረገድ ዉሉን በመካድ መከራከራቸዉን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ጉባኤዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ዉድቅ በማድረግ በፍሬ ነገር ላይ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገዉ ዉል እንዲፈርስ አመልካቾች ዳኝነት ጥያቄ አላቀረቡም በሚል ምክንያት በዉሉ መሰረት መሬቱን ለማስረከብ እና ዉክልና ለመስጠት ይገደዳሉ በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ ይህንኑ ዉሳኔ ለማስለወጥ ነዉ፡፡የአመልካቾች ጠበቃ አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የእሽሙር ሽርክና ማህበር እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረባቸዉን ጠቅሰዉ አመልካቾች ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በጉባኤዉ ዉድቅ መደረጉ ያለአግባብ መሆኑን፤የእሽሙር ሽርክና ማህበር ዉል የለም እንጂ ዉል አለ ቢባል እንኳን በዉሉ አንቀጽ 6 መሰረት በተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባት የተፈጠረ እንደሆነ በስምምነት ለመፍታት ካልተቻለ በአዲስ አበባ ንግድ ም/ቤት በሚመደብ ሶስት የግልግል ዳኛ ዉሳኔ ያገኛል ተብሎ እያለ አንድ ዳኛ ጉዳዩን ማየቱ ከቀረበዉ ስምምነት ዉጪ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፤በስረ ነገር ረገድ ጉዳዩ የይዞታ ጉዳይ ስለሆነ የግልግል ጉባኤ ስልጣን የለዉም፤ተጠሪ ጠበቃችን ስለነበረ ካለዉ ግንኙነት አንጻርና ዉሉ መሬት የመሸጥ ዉጤት ስላለዉ ህገወጥ ዉል ነዉ ተብሎ እንዲፈርስ በማለት አመልክተዋል፡፡የአመልካቾች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ለክርክር መነሻ የሆነዉን የእርሻ መሬት በጋራ ለማልማት በሚል የእሽሙር ሽርክና ማህበር የተባለዉ ሲመሰረት አለመግባባት ሲፈጠር በንግድ ም/ቤት በሚመደብ ሶስት የግልግል ዳኛ ዉሳኔ እንደሚያገኝ የተስማሙ ስለመሆኑ ጥር 10 ቀን 2010ዓ.ም በተደረገዉ ስምምነት ላይ በተገለጸበት ጉዳዩ በአንድ የግልግል ዳኛ ብቻ ታይቶ አመልካቾች የእርሻ መሬት ይዞታቸዉን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ፤ንብረቱን በሚመለከት ተገደዉ ዉክልና እንደሰጡ የተወሰነበትን አግባብነት ከህገ መንግስቱ እና ከፍ/ብ/ህግ ድንጋጌዎች አንጻር መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት አዟል፡፡የተጠሪ ጠበቃ በቀን 17/09/2014ዓ.ም ጽፎ ባቀረበዉ መልስ አመልካቾች ተገቢዉን ዳኝነት ሳይከፍሉ ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት እንደሌለዉ፤ጉዳዩ ዉስብስብነት የሌለዉ በመሆኑ ለተፋጠነ ፍትህ ሲባል በአንድ ዳኛ እንዲታይ መደረጉ በስምምነታቸዉ መሰረት መሆኑን እና በአንድ ዳኛ መታየቱ መሰረታዊ  የህግ ስህተት አለመሆኑን እንዲሁም በፍሬነገር ረገድ የቀረበዉን ክርክር ሰበር ችሎቱ የመመርመር ስልጣን የለዉም በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካቾችም አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል ጥር 10 ቀን 2010ዓ.ም የተደረገ ዉል ሲሆን ጉዳዩ በመጀመሪያ በግልግል ጉባኤ የታየዉም ይህንኑ ስምምነት መሰረት በማድረግ መሆኑን እና በግልግል ጉባኤ ዉሳኔ ላይ በቀጥታ ለሰበር ችሎት አቤቱታ ሊቀርብ የቻለዉ በግልግል ጉባኤ የሚሰጥ ዉሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ ስምምነት መደረጉን ተከትሎ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡የአመልካቾች አቤቱታ በጥቅሉ ሲታይ የጉባኤ ዉሳኔ ስነስርዓታዊ እና የስረ ነገር ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚል ነዉ፡፡ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የቀረበበት አንደኛዉ ጭብጥ ክርክሩ በአንድ የግልግል ዳኛ መታየቱ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ነዉ፡፡እኛም የስረ ነገር ክርክሩን ከመመመርማራችን በፊት ጉዳዩ በአንድ የግልግል ዳኛ መታየቱ ተገቢ መሆን አለመሆኑን እና በዚህ ነጥብ ላይ ሰበር ችሎቱ መርምሮ የመወሰን ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን በቀዳሚነት መርምረናል፡፡

በህግ በሌላ ሁኔታ ካለተገደበ ወይም ካልተከለከለ በስተቀር ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸዉ የተፈጠረ ወይም የሚፈጠር አለመግባባት ከፍርድ ቤት ዉጭ ባለዉ አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገድ አመግባባቱ እልባት እንዲያገኝ የመዋዋል ነጻነት አላቸዉ፡፡አለመግባባቶች ከፍርድ ቤት ዉጪ ባለዉ አማራጭ የክርክር መፍቻ መንገዶች እንዲታዩ ተመራጭ ከሚሆንባቸዉ ምክንያቶች ጥቅቶቹ በዘርፉ በቂ እዉቀትና ልምድ ያለዉ ባለሞያ ወይም ተቋም ለመምረጥ፣ሚስጥራዊነትን መጠበቅ፣የተፋጠነ እና ዉጤታማ ዉሳኔ ለማሰጠት እንደሆነ ይታመናል፡፡በተለይ ደግሞ የግልግል ተቋማት እና የግልግል ዳኛ ምርጫ በተከራካሪ ወገኖች ነጻ ፈቃድ የሚደረግ በመሆኑ ለዚህ ሰፊ እድል የሚሰጥ መሆኑ ይታወቃል፡፡ለዚህም ሲባል በግልግል አካል በሚሰጥ ዉሳኔ ላይ የመደበኛ ፍርድ ቤቶች ሚና ወይም ወደ ፍርድ ቤት የሚቀርብ ቅሬታ ወይም ይግባኝ በጊዜም ሆነ በይዘቱ በዉስን ጉዳዮች ላይ ብቻ ተደርጓል፡፡የግልግል ጉባዔ ወይም በቤተ ዘመድ በሽምግልና ዳኞች ዉሳኔ ወይም ብይን ላይ ይግባኝ በሚቀርብበት ወይም ብይኑ እንዲሻር (setting aside arbitral award) አቤቱታ የሚቀርብበት ምክንያት እና የጊዜ ገደብ የተለያዩ መሆኑን የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 350(3)፣351 እና 355 ድንጋጌዎች ይዘት ያሳያል፡፡

ከዚህም መገንዘብ የሚቻለዉ በግልግል ጉባኤ ዉሳኔ ወይም ብይን ላይ ይግባኝ እና የማሻር ጥያቄ የሚቀርብበት ስርዓት በተለየ ሁኔታ የተደነገገ ስለመሆኑ ነዉ፡፡ይኸዉም የግልግል ዳኞች በሚሰጡት ዉሳኔ ለፍርድ ቤት የሚቀርበዉ አንድም በመደበኛ ይግባኝ /Appeal/ ዓይነት ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ ፍርዱን ወይም ብይኑን የማሰረዝ/የማሻር/ አቤቱታ/setting aside of award/ በሚል የተከፋፈለ ስለመሆኑ

የድንጋጌዎቹ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ የፍ/ብ/ስ/ስ/ ቁጥር 350(2) በተለይ ሲታይ ደግሞ ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ጉባኤ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል ወይም ይግባኝ የማይበልበት ይሆናል በሚል በግልጽ መስማማት ይችላሉ፡፡በዚህ መሰረት ከተስማሙ በማናቸውም ምክንያት በፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 351 ላይ የተዘረዘሩትን ምክንያቶች ጭምር መሰረት በማድረግ ይግባኝ ማቅረብ አይቻልም፡፡ተዋዋዮቹ በግልግል ዳኝነት ስምምነታቸዉ ይግባኝ መብት ቀሪ ካላደረጉ ግን በፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 351 ስር በተመለከቱት ምክንያቶች ላይ በመመስረት ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ይህ ሲባል ግን መሰረታዊ የህግ ስህተት በሚመለከቱ የህግ ክርክሮች ላይ አቤቱታ ለሰበር ማቅረብን የሚያስቀር አለመሆኑን ሰበር ችሎቱ አስገዳጅ ዉሳኔ የሰጠበት መሆኑ ልብ ይለዋል፡፡ሰበር መ/ቁ/42239 በቅጽ10 ላይ የታተመዉን ይመለከቷል፡፡በሌላ በኩል የግልግል ዳኝነት ዉሳኔ ለማሻር(setting aside of award) አቤቱታ ማቅረብ የሚቻልባቸዉ ምክንያቶች የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 356 ደንግጓል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል በተደረገዉ ዉል ላይ የሚፈጠር አለመግባባት ሶስት የግልግል ዳኞች በተሰየሙበት እንደሚታይ ስምምነት የተደረገ መሆኑ አላከራከረም፡፡ ይሁንና ጉዳዩ የታየዉ በአንድ የግልግል ዳኛ ስለመሆኑ የስር መዝገብ ይዘት ያሣያል፡፡ አመልካቾች ቅሬታም በአንድ የግልግል ዳኛ መታየቱ ከስምምነታቸዉ ዉጭ ነዉ የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ጉዳዩ በአንድ የግልግል ዳኛ የታየዉ ዉስብስብ ባለመሆኑና የተፋጠነ ዉሳኔ ለመስጠት ነዉ በሚል ተከራክሯል፡፡ከመዝገቡ እንደተረዳነዉ ክርክሩ በአንድ ዳኛ እንዲታይ የተደረገዉ በአንድ ዳኛ ቢታይ ተብሎ በግልግል ጉባኤ የቀረበዉን ሃሳብ አመልካቾች አልተቃወሙም በሚል ምክንያት ስለመሆኑ ብይኑ ያሣያል፡፡ስለሆነም ጉዳዩ በአንድ ዳኛ መታየቱ አከራካሪ ባይሆንም በአንድ ዳኛ እንዲታይ የተሰጠዉ ብይን ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን ከስምምነታቸዉ እና ከህጉ ጋር በማገናዘብ መመርምር ያስፈልጋል፡፡ይህ ደግሞ ሊታይ የሚችለዉ የግልግል ጉባኤ የሰጠዉን ብይን ለማሰረዝ ከሚቀርቡ ምክንያቶች አንዱ የግልግል ዳኞች ቁጥር በግራ ቀኙ ስምምነት ከተደረገበት ቁጥር ያነሰ ወይም ሌላ የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 355(1) እና 356(ለ) ድንጋጌ ይዘት ያመላክታል፡፡በፍ/ብ/ህግ ቁጥር3325 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እንደተመለከተዉ ጉዳዩ በገላጋይ ዳኛ እንዲወሰን ግራቀኙ የተስማሙ እንደሆነ ገላጋይ ዳኛ የመመረጥም ሆነ ቁጥሩን የመወሰን መብትም የራሳቸዉ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህም ጉዳይ የግልግል ጉባኤ ዳኝነት ስልጣን ምንጩ የተዋዋይ ወገኖች ስምምነት መሆኑን መዝገቡ ያሣያል፡፡ስለሆነም የግልግል ጉባዔ ዉሳኔ የሰጠዉ ባልተሟላ ዳኛ ነዉ የሚለዉ የአመልካቾች ቅሬታ ነጥብ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 355(1) እና 356(ለ) መሰረት የግልግል ዳኝነት ጉባኤ(ገላጋይ ዳኛ) ዉሳኔ ማሻር (setting aside) አቤቱታ

ሊቀርብበት የሚችል እንጂ በይግባኝ /Appeal/ ስርዓት የሚታይ አይደለም፡፡በዚህ አግባብ የገላጋይ ዳኛዉን ዉሳኔ የማሻር አቤቱታ የሚቀርበዉም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር355(2) እና 352 መሰረት ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ታይቶ ቢሆን ኖሮ ከመጀመሪያዉ ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚመለከተዉ ፍርድ ነዉ፡፡

በዚህ ስነስርዓት መሰረት የማሻር አቤቱታ ቀርቦ በህግ ስልጣን ለተሰጠዉ ፍርድ ቤት አመልካቾች አቤቱታ አቅርበዉ የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ባለመኖሩ በሰበር ችሎቱ ሊመረመር የሚችል አይደለም፡፡እንደሚታወቀዉ አንድ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በሚል ለሰበር ሰሚ ችሎት የሚቀርበዉ ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ ካገኘ በኋላ ስለመሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ በግልጽ ደንግጓል፡፡(አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/5፣2/4 እና 10 ይመለከታል)፡፡የመጨረሻ ዉሳኔ ነዉ የሚባለዉ በፍርድ ቤት፣በህግ የመዳኘት ስልጣን በተሰጠዉ አካል፣በተቋማት ወይም በአማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴዎች የተሰጠ እና ለጉዳዩ እልባት የሚሰጥ ፍርድ ፣ብይን ትእዛዝ፣ዉሳኔ እና /ወይም የይግባኝ ሂደቶችን የጨረሰ ፍርድ፣ብይን፣ትእዛዝ ወይም ዉሳኔ ስለመሆኑ በአንቀጽ 2/5 ስር ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡በተያዘዉ ጉዳይ በስረነገር ረገድ የግልግል ጉባኤ የሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ ስምምነት አድርገዋል፡፡ይህ ስምምነታቸዉ ገደብ የሚጥለዉ በይግባኝ መብት ላይ ነዉ፡፡በፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 355(1) ስር እንደተደነገገዉ በዚህ መልኩ የይግባኝ መብት ለማስቀረት የሚደረግ ስምምነት የግልግል ዳኝነት አካል ዉሳኔ የማሻር አቤቱታ (setting aside of award) ከማቅረብ የሚከለክል አይደለም፡፡አመልካቾችም ይህንን ስርዓት ተከትለዉ የማሻር አቤቱታ ማቅረብ ሲገባቸዉ የስነስርዓት ጉድለትን እና የስረነገር ክርክሩን በአንድነት ማቅረባቸዉ ተገቢ ሆኖ አላገኘንም፡፡በተለይም ከገላጋይ ዳኛ ቁጥር ጋር በተያያዘ የተነሳዉ ቅሬታ የግልግል ዳኝነት ዉሳኔ በማሻር ስነስርዓት (setting aside procedure) ስርዓቱን ጠብቆ እልባት ባላገኘበት ሁኔታ ጉዳዩ የመጨረሻ ዉሳኔ አግኝቷል ሊባል ስለማይችል በዚህ ደረጃ በስረነገር ረገድ የቀረበዉን ክርክር መመርመር ተገቢ ሆኖ አላገኘንም፡፡

ስለሆነም አመልካቾች በስነስርዓት ረገድ ያነሱትን ቅሬታ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ሳያስወስኑ እና ጉዳዩ የመጨረሻ ዉሳኔ ሳያገኝ ለሰበር አቤቱታ ማቅረባቸዉ የክርክር አመራር ስርዓትንም ሆነ የሰበር ችሎቱን ስልጣን ያገናዘበ ባለመሆኑ አቤቱታዉ ለሰበር ብቁ አይደለም ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ትእዛዝ ሰጥተናል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

**በጉባዔዉ ዉሳኔ ላይ የማሻር አቤቱታ ስልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት ማቅረብን ይህ ዉሳኔ አያግድም፡፡**

**ጉዳዩ የመጨረሻ ዉሳኔ ሲያገኝ የሰበር አቤቱታ ማቅረብን ይህ ዉሳኔ አያግድም ብለናል፡፡**

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤትይመለስ፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ሰ/ጥ**